.. መታደል እንጂ መታገል አያሻም
.. አህያ የሚነችውን ፈረስ ይበላል
.. መብሉ ላሞራ ጩኸቱ ለቁራ

390. መጥ ማየይ ዴእሽን ገርጥ ማየይ አዩስ
. ለፍቶ የሰበሰበ እያለ ተውሶ የለበሰ ይኮራል
.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
.. የተውሶ ይሄዳል ተመልሶ
.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

391. መጥ ስክንከ መጨቴት መጨቴታ
. ሰብስበው ቢሰፉትም የሴት ብልት ያው ነው
.. ምን ቢያጣምዱ በዘጠና ከቤት አይወጣ ቀጠና
.. ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

392. መጥኔ ሃታ ዋደን ቢድ ሃተ ክዩስ
. ጨው ውሃ ሊዋኝ ሄዶ ራሱ ውሃ ይሆናል
.. አተርፍ ባይ አጉዳይ
.. አቅሙን አያውቅ

393. መጥኔ ሎኦ ጋነው መራዮ ዎሬስ ኢተ ጋነው ባክዮ ማቴስ
. ሶግዳ (ሆራ) ጥሩ ነው እንዳይባል ባለ ጥጃዋን ይገድላል ክፉ ነው እንዳይባል ወተት የነፈገችውን እንድትታለብ ያደርጋል
.. ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጇ ሆነባት

394. መጥኔ በው ሃተሽን ሃታ ወደነው ሻፋ ቤስ
. ጨው ለራሱ ውሃ ሆኖ ግን ለዋና ወንዝ ይሄዳል
.. ከእጅ አይሻል ዶማ
.. አቅሙን አያውቅ
.. አሞሌ ሲወፍር ወንዝ አውርዳችሁ እጠቡኝ ይላል
.. ከወፈሩ ሰው አይፈሩ

395. መጥኔ በይነን ከት መልኤነ፣ ማሰር በይነን ኦል ስሜነ

. ጨው የሌለበት ምግብ አይጣፍጥም

ማስሬ (ዘር) የሌለበት ጦርነት አይመለስም

.. ቤት ያለሴት በረት ያለከብት

396. መጥኔ ከልድ ሃታ ወጼስ

. ጨው ሲ.ጠግብ ውሃ ይዋኛል

.. ከወፈሩ ሰው አይፈሩ

.. የጠገበ አበደ

.. የጠገበ ሰው ራሱን አያስብም

.. አሞሌ ሲ.ወፍር ወንዝ አውርዳችሁ እጠቡኝ ይላል

397. መጤነይ ሙጤነን ምቴስ

. ያላፈራ ሳይመትር ይውጣል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. የሰው ነገር አለመናገር

398. መጨ ነኣስ በንገይ በሸየን ናኣ ምጭዮጌ ፖኮ

. ለሴት ልጅ ገብስ ምጣድ ላይ ሁለቴ ካረረ ነውር ነው

.. ከስህተቱ የማይማር

.. አድሮ ቃሪያ

399. መጨ ነኣስ በንግ ናአ ምጭዮጌ ፖኮ

. ለሴት ልጅ ገብስ ሁለቴ ካረረ ሞት ነው

.. የሴት ከርፋፋ እቃውን በዕቃ ደጋግፋ፣ አንዱን ስታነሳ ሁሉም ይደፋ

400. መጨ አሰይ ደርዮ ኬተን ሰንተይ ከኤነን ክዩስ

. ሴት በበዛበት ቤት ጐመን ሳይበስል ይወጣል

.. ሴት ከበዛ ጐመን ጠነዛ

401. መጨ አሰይ ደርዮ ዎዲየን ዘሬ ገማ ኤሴስ

. ሴት በበዛበት እንሽላሊት ጭገር ያቆማል

.. ፈሪን የሚያባርር አይጠፋም

.. በሴት የማይበረታ የለም

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

402. መጨ አሰይ ደሮሳን ሰንተይ ሀልቁሜስ

. ሴት በበዛበት ቦታ ጎመን ይጠነዛል

.. ሴት ሲበዛ ጎመን ጠነዛ

403. መጨ አሳ ኤራ፣ መግላላ ቀራ ጌቴስ

. የሴት ዕውቀት፣ የመቅላ ስለት

.. ሴት የመከረው ሞት አይፈራም።

404. መጨ አሳዮ ቡቻ ሞኩዋ ድገይ ጨዴ ፖኖ

. ሴትን ዒም የነሳት የጎደሬ ቅጥቅጥ መቆንጠር ነው

.. ሴት ባትዋሽ ባሏን ትወልዳለች

.. የሴት ብልሃት የጉንዳን ጉልበት

405. መጨ አሰ፣ ሀይቀ አሳ ጌቴስ

. ሴት ሰው፣ ሙት ሰው እንደ ማለት ነው

.. ሴት አሉሽና ምን ይበሉሽ

.. አባም ሰው ሆኑና ሰው ገደላቸው

406. መጨ አስ ደርዶ ሶን ሀለኮይ ቀዩ ክዩስ

. ሴት በበዛበት «ሽፈራው» ሳይበስል ይወጣል

.. ሴት ሲበዛ ጐመን ጠነዛ

407. መጨራረ ዴእየ አፈላ ኪስን መል በይን አስ ማዩስ

. ፈርጅ ያለው ነጠላ አሰርቼ መልክ የሌለው ሰው ይለብሳል

.. ነገር ያለቦታው ሆነና ቸገረኝ...

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

.. የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ያቼን ላንቺ ማን አለሽ

408. መጨቴታ ሀርግያ አቱመቴተይ ኤርኪ ጌስ

. የሴትን ብልት በሽታ የወንድየው ብልት አላውቅም ይላል

.. ያንዱ ችግር ለሌላው የእንጀራ ልጅ ነው

409. መጨቴታ ነገረይ ሀርያረ ዝንእሲስ

. የሴት ጡር ከአህያ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ያስደርጋል

.. የውሃ ጡር በእድፍ ያስታጥባል

410. መጨቴታ ኤሬናጋው ጉልአ ቢሰውሱ

. ብልት ለማያውቅ እንብርት ታሳያለች

.. ሞኝ ያውቃል ቢሉት በሬ ይወልዳል ወይ አለ

411. መጨቴታ ዳፋይ ዱሌስ አቴስ

. የብልት ሃጢአት ለቂጥ ይተርፋል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

412. መጨቴት ገጭኖ አይቸነ በይስ ጊድ አግየን ጉልበታ ሜቂስ

. የሴት ብልት እመጫት ጥየቃ ሲሄድ መንገድ ላይ ጉልበቱን ይሰበራል

.. የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች

413. መጫሰይ መቅዶሰን ማት ዶሌነ

. ሴት የመከረችበት ሳር አይበቅልም

.. ሴት የላከው ሞት አይፈራም

414. መጫሰዮ ዎሲነን ላዘንታ ዬዴስ

. ሴት ሳያጭ ጥሎሽ ይልካል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምባው ቀጢጥ

415. ማህያ ቀንተን ገወረይ ዬሌቴስ

. ከነብር ማህፀን ድመት ይወለዳል

.. የናት ሆድ ዥንጉርጉር

416. ማህያ ኡሉወን ዜሩሰይ ዝንኢስ

. ከነብር ማህፀን አነር ይፈጠራል

.. የናት ሆድ ዥንጉርጉር

.. ፍየል መንታ ወልዳ አንዱ ለመጣፍ፣ አንዱ ለወናፍ

417. ማሄ ሃታ ኡይዮሳ ኦኔ ኤሬነ

. ነብር ውሃ የሚጠጣበትን ስፍራ ማንም አያውቅም

.. ሙያ በልብ

418. ማሄ ምዮ ለይት ገረወይ አይፍያ ኬሴስ

. ነብር ሰው በሚበላበት አመት ድመት አይን ያፈጣል

.. የዘሬን ብትው ያንዘርዝረኝ

.. ዘር ከልጓም ይስባል

.. ነብር ባየለበት ዘመን ድመት ጭገር ያቆማል

419. ማሄ አሰው የይሽን አሰይ ማህየው የይሽን ኦጌ ሜለ አቂስ

. ነብር ለሰው ሲፈራ ሰው ለነብር ሲፈራ መንገድ ባዶውን ያድራል

.. ትልቅ መንግድ ሰው ጅብ ይሄዳል ሲል ጅብ ሰው ይሄዳል ሲል ጦሙን ያድራል

420. ማሄ ዘማንድ ዴርየን ዴሻ ሄሜስ

. የሚያስደንቅ ነገር ዱር ነብር ፍየል ያግዳል

.. የቀበሮ ባህታዊ ከበጐች መካከል ይፀልያል

421. ማሄ ዴሽ ሂሚ? መጥኔ ሃታ ወጺ

. ነብር ፍየል ያግዳል? ጨው ውሃ ይዋኛል?

.. ዘመነ ግልምቢጥ ውሻ ወደ ሰርዶ፣ አህያ ወደ ሊጥ

422. ማሄ ኀይነ አይቆፐ አይቅኮኔ ዩዶፐ

. የነብርን ጅራት አትያዝ፤ ከያዝከም አትልቀቅ

.. የነብርን ጅራት አይይዙም ከያዙም አይለቁም

423. ማሄ ጭምን ኡዱንጤ አይፍየን ጉፔስ

. ነብር ሲያረጅ ዝንብ አይኑ ላይ ይጨፍራል

.. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል

424. ማሄ ጩግድ ዜሩሳ ዩሌስ

. ነብር ሲያረጅ አነር ይወልዳል

.. መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል

425. ማለረሻ በረየቶ መይኔ፣ በሸይኔ፣ ሀእዌ ዩሲዩ ጨሸቺ ገውሱ

. የማላን ባላባት ባዝራ በላሁም፣ ተውኩም፣ ያሁኑ ያስለ ቅሳል ወይስ አለች

.. ያልፈሳሁበት ዳገት የለም

426. ማለዶ መንደርዳጋ ቆልቻወይ ገኬነ

. ማልዶ በእግሩ ጉዞ የጀመረውን ባለፈረስ አይደርስበትም

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

427. ማለዶ ማጣነን መንደርዳጋ አመርስ ቆልቻወይ ገኬነ

. ማለዳ በጌኛ ጉዞ የጀመረውን ማታ በሰንጋ ፈረስ የተጓዘው አይደርስበትም

.. ትዳርና መንገድ በጥዋት ነው

.. ትምህርት በልጅነት፣ አበባ በጥቅምት

428. ማለዶ ማጣነን ኦመርስ ኦዶልቸን

. ጥዋት በጌኛ ማታ በሰንጋ ፈረስ

.. እድሜ መስተዋት ነው

429. ማለዶ ቀንኤ ደንጋርሳ ፔሼስ

. የማለዳ ቁርስ ዝሆንን ያውላል

.. ያወቀ ዘለቀ፣ ያላወቀ አለቀ

.. የምግብ ትንሽ የለውም

.. ሆድ ባዶ ይጠላል

.. በቁርስ ዋዛ ምሳ ይመስል

430. ማላ እጥዳረ መናፔ እዴጠውሱ

. ደህናውን እንቢ ያለች ከሸክላ ሰሪ ታረግዛለች

.. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

431. ማላፔ ዴጌል ሎኦ ጌቴስ

. ከጨዋ ሰው ፋቂ ይሻላል ይባላል

. ከማላ በመልክ ፋቂ ይበልጣል ይባላል

.. ጥሎ አይጥል

432. ማሎ ከንያ ቦሮዳ ከሪየን ሽያ ሽየውሱ

. የማሎ ባላባት ውሻ ቦሮዳ ደጅ ታራለች

.. ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች

433. ማሎ ኮሌ ቃለ መነ ነኣ ቈርጾይ ኤሬስ

. የማሎ ኩሌን ቋንቋ የማና ልጅ ቈርጾ ያውቃል

.. እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ

.. ስንተዋወቅ እንተናነቅ

434. ማሎ ፐርሶይ ኡዳላ ቦንቅሲስ

. የማሎ ሬ ላ ሙቀጫ ያስነጥቃል

.. የጠገበ አበደ

.. የጠገበ ሰው ራብን አያስብም

.. የጥጋብ ብዛት ያደርሳል ከሞት

435. ማመዱ ጠልያ ኡይን አርጎዞ ጌዩስ

. ማመዶ ኮሶ ቢጠጣ አርጎዞ ያሸረዋል

.. አባ ኮሶ ጠጥተው እማሆይ አሻራቸው

.. አቃቢት በተልባ በበላች ገበዙን ተጋረፈው

436. ማር ማኀ ኤክን መቀ ቡች አዋስ ጋምኤስ

. ማሬ ባልሰራበት ሲመሰገን የአገዳ አጨዳ የአባቱ ስራ (ድርሻ) ይሆናል

.. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ

.. እድል ነው ወይስ በደል

437. ማሬቴነን ዎርደ መይራሞ ዎስዮጌ ዎጌ?

. በምጥ የገደለችውን ማርያምን መለመን አግባብ ነውን?

.. ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል በቶሎ

438. ማተይ በይነሰን ኦይተይ ዴኤስ

. ወተት በሌለበት ቂጣ አለ

.. ማማው ሞረት ማሽላው ቅምብቢት

.. ፍየሏ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. ሀራምባና ቆቦ

439. ማተይ ዴእዮ ኪታወይ ኀድሽን ፔኤስ

. መብት ያለው ሰው ሲያሳድዱት እምቢ ብሎ ይኖራል

.. አንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ተናግሮ

440. ማተይ ዴእዮ ኪታውስ ብረሰ ኡስያ ገከውሱ

. ለባለወተት እርጉዝ ጊደር ትደርሰዋለች

.. ላለው ይጨመርለታል

441. ማታ ማቱዋ ቶሪ ዛሬስ

. የወተትን ስካር ጦር ይመልሳል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. የጥጋብለት ሁሉ አንበሳ

.. የሰከረ አወዳደቁ አያምር

442. ማታ ቡክያረ ዩሱዋ ኡይኮ ኦይሳ ኦኔ ደገየነይ

. ወተት የምትንጥ ትኩስ ወተት ከጠጣች ቅቤ ማን ያጠራቅማል

.. ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ

443. ማታ ቡጫጌ ዴእሸን ኡታጌ ኡስቴስ

. ሣር ያጨደ እያለ የተቀመጠ በወተት ይበላል

.. ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

.. አህያ የተሸከመውን ፈረስ ይበላል

444. ማታ ኡይደ ከነይ ሱራ ሚደ ሀርያ ዶነን ቂጩስ

. ወተት የጠጣ ውሻ ሰርዶ በበላ አህያ አፍ ይጠርጋል

.. የእምዬን ወደ አብዬ

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

445. ማታ ኡይደ ከንያ ኦይሳ ትዩነን ቢኬ ገውሱ

. ወተት ያጠጧት ውሻ ቅቤ ሳትቀቡኝ አልሄድም ትላለች

.. ስንዝር ሲሰጧት ጋት ጨምሩልኝ ትላለች

.. እፀድቅ ብዩ ባዘላት ተንጠልጥላ ቀረች

446. ማታ ኡዩነ አስ አሉወን ሀይቂስ

. ወተት የማይጠጣ ጠይብ በግልግል ቦታ ይሞታል

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

.. ለገላጋይ ደም የለውም

447. ማታ ኡዩነይ አሉዋ ቶራን ሀይቄስ

. ወተት የማይጠጣ በግልግል ጦር ይሞታል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. መብሉ ላሞራ ጩኸት ለቁራ

.. ያለዕዳው ዘማች ዋ ብሎ መቅረት

448. ማታ ኡዮ ኢ.ታፔ ዶና ቁጬናጌ ፐለቴስ

. ወተት ከመጠጣቱ አፍ አለመጥረጉ ያሳፍራል

.. ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይመቱም

.. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁም

449. ማታ እጠነ ሚዝያ ማታ እጠውሱ

. ወተት ልትከለክል ያሰበች ላም ሣር አልበላም ትላለች

.. አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

450. ማታ ድገነ ሚዝያ እመታ ቶረን ዲሼተውሱ

. ወተት ልትከለክል ያሰበች ላም በእንግዳ ጦር ላይ ትታከካለች

.. ስንተዋወቅ እንተናነቅ

.. አያጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

451. ማታው ነኣረ ገይቶፐ፣ ፐራው ነአረ ዘቶፐ

. ከባለ ወተት ልጅ ጋር አትዋል፣ ከባለ ፈረስ ጋር አትጓዝ

.. አቅምህን እወቅ

452. ማታዬ ነኣኔ ድምቡዋዬ ነኣኔ ፑዴተይ ሻኮ

. የባለወተቷን ልጅና የባለቦርዴዋን ልጅ ዳገት ይለያቸዋል

.. ሆድን በጐመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል

453. ማታዬ ነኣኔ ፐርሱዋዬ ነኣኔ ፑዴተን ፓጨነ

. የባለወተቷን ልጅና የባለመሸታዋን ልጅ ዳገት ላይ እንታዘባለን

.. የበላ ቢያብል ሰውነቱ ይናገር

.. ሆድን በጐመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል

454. ማነ ጊሽን መልአ ቁመይ አቴስ

. ጣፋጭ ምግብ እበላለሁ እያሉ ይቀራል

.. ምኞት ያከሳል

.. ከእጇ በጉንጩ

455. ማነ ጎሮሞትያ ሎሜ ገውሱ

. የምትበላ ቡዳ ፍቅርዬ ትላለች

.. ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ይሿታል ጅግራ

.. ላያውቋሽ ታጠኝ

456. ማነ ጎሮሞትያ ተምቼ ገውሱ

. የምትበላ ቡዳ እህቴ ትላለች

.. ላያውቋሽ ታጠኝ

.. ሌላ ብዬ

.. ጠርጠር ከምግብ ውስጥ አለ ስንጥር

457. ማነ ጢሌ ኡስተነ ማተን ጉኪስ

. የሚበሉት ዱቄት በማማጊያ ወተት ላይ ይፈሳል

.. ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

458. ማነው ኤቅዶ ማትዮ ሰንተ ጌቱስ

. ለመብላት ያሰቧትን ሳር ጐመን ይሿታል

.. ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ይሿታል ጅግራ

459. ማነው ጠይደ ኦይሰይ ሀይቅን ሲርየረ ጎጊስ ጌስ ኩቶይ

. ለመብላት የጠፋ ቅቤ ስሞት በአፍንጫዬ ይፈሳል ይላል ዶሮ

.. ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ

.. በቁም ያልረዳ ዘመድ ሲሞቱ አርባ ይደግሳል

460. ማናፔ መ መ ጉስ ኢተ

. ከመብላት ብላ ብላ ማለት ይከፋል

.. ማድረግና ማሰብ ለየቅል

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

461. ማየነው በይናጌ ጉሌታ አሞቴስ

. የሚለብሰው የሌለው የሚከናነበውን ይመኛል

.. የምታጠልቀው የላት የምትከናነበው አማራት

462. ማየነው በይናጌ ጨወው ኮዬስ

. የሚለብሰው የለው የላብ መጥረጊያ ይፈልጋል

.. የምታጠልቀው የላት የምትከናነበው አማራት

463. ማይዶበን ቡሉኮይ ሆኦ ባርኖሲ ሆኦ ግን ሚጭን ውሬቼስ
ማይደበን መቾ ሆኦ ጌስ

. ከሚለብሱት ነገር ቡልኮ ይሞቃል ወይስ በርኖስ ቢሉት ታጥቦ ያልቃል ከሚለብሱት ነገር ሚስት ትሞቃለች ይላል

. ሚስትና ዳዊት በብብት

.. የሚጠቅመውን ባለቤቱ ያውቃል

464. ማይዮይ ዳንጭዮይ ባወሽን ቦንቾይ ጌሬሮ ጎዳ ጌቴስ

. የሚለብሰውና የሚታጠቀው የሌለው ሰው የጌሬሮ ጌታ ይባላል

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

.. መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ

465. ማዮይ ዴእዮረ ከነ ገጭኑዋ አንጀውሱ፣
ማዮይ በይነ ምሽርያ አሰ ገጭኑዋ አንጂኩ

. ልብስ ያላት የውሻ እመጫት ስትጠይቅ ልብስ የሌላት የሰውን እመጫት ሳትጠይቅ ትቀራለች

.. ያለው የእንጀራ እናቱን ተገኳር ሲያወጣ የሌለው የናቱን ያስተጉላል

466. ማዮይ ገርቴ ግዴነን አጌነ፣ ስመ ስመ ጤለውሱ ጌዶይ ጉተ
ግዴጉን አጌነ ሰበሰበ ዬከውሱ

. ልብሱ የተውሶ ነው መሰለኝ እየዞረች ታያለች፣ ባርነት አለባት መሰለኝ ደጋግማ ታሞግሳለች

.. ፊስ ያለበት ዝላይ አይችልም

.. ብልጥ የሚታወቅበት አይመስለውም

467. ማደ ሚኪ ግየ ልምአ ቀጠኔ

. በልታ አልበላሁም የምትል ዋሾ ቀጠና

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

.. አፍ ቢያብል ልብ ዳኛ ነው

468. ማዴነ መይራመ ገለስ ጥስክሰውሱ

. የማትረዳ ማርያም ቀን ለቀን እንቅልፍ ታመጣለች

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው

.. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

469. ማጠነ አይያ ዴእሽን መረይ ዳሬስ

. የምትታለብ እናት እያለች ጥጃው ያላዝናል (ያጓራል)

.. የእምዬን ወደ አብዬ

.. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

470. ሙልጨይ ጥንቂዋን ጋሶቴስ

.ሞጭሚጫ በስንጥር ይሳበባል

.. ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት

.. እንኳን ዘንቦብሽ ዱሮም ጤዛ ነሽ

471. ሙሌ በይናጌ ጩምኡ ግን ማገነ ጌስ

. ምንም የሌለው ቅቤው ሲንጠባጠብ እበላለሁ ይላል

.. የምትለብሰው የሌላት የምትከናነበው አማራት

472. ሙሌ አገነይ ዝንኡወን ዞሬቴስ

. ጭራሽ ሊተው መኝታ ላይ ይማከራል

.. አይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች

473. ሙሳ ደሮይ ሜራ ኪሴስ

. መብላት መልክ ያወጣል

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

474. ሙቅያ በነ ከሜነን ዛላ ከመውሱ

. ቢራቢሮ ለራሷ የማይበቃትን ክንፍ አለት ድንጋይ ታለብሳለች

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

475. ሙቆይ በርነ ገኪነ ቁፍያ ዛላ መይዜስ

. ቢራቢሮ የራሱን ገመና መሸፈን የማይችለውን ክንፍ ንጣፍ ድንጋይ ያለብሳል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

476. ሙጃሌ ሚዶ ጌዴ ጫማ ከጀሌስ

. ሙጃሌ የበላው እግር ጫማ ይከጅላል

.. አህያ ኮርቻ ተመኘች

.. አቅሙን አያውቅ

477. ሙጦ ኤሬነይ በርሶ ኤሬስ

. መምተር የማያውቅ ማጉረስ ያውቅበታል

.. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ

.. በሰው ቂጣ እጅዋን ትቃጣ

478. ም ም ዩሽን መሸ መሸ ጌስ

. እየጠገቡ ሲመጡ ብረት ብረት ይላል

.. ሲበዛ ማር ይመራል

479. ም ቤእዶ ምታ ገርሰን ኡትድ ቦለው ጤሌቴስ

. የበሉበት ዛፍ ስር ተቀምጦ ወደ ላይ ያዩዋል

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

480. ምልአይ ም አቄስ

. አይን አውጣ (ብልጥ) በልቶ ያድራል

.. ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም

.. አፍ ያለው ያግባሽ ከብት ያለው ያግባሽ እንዲሉ

481. ምልኬ ሚዛፔ ሎአ

. ደግ ነገር መመኘት ከከብት ይሻላል

.. መልካም ተመኝ መልካም እንድታገኝ

482. ምሊጦይ ከልታ ኤክድ ምታ ቁረነው ሻፋ ቤስ

. ሹጥ መጥረቢያ ይዞ እንጨት ለመቁረጥ ወደ ወንዝ ይወርዳል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

483. ምሊጦይ ጌድያ ቦል ዴእዮ ነእዮ ሚዛ ሄምየ ሾላ ነአይ አይቼስ

. ሹጥ እግሯ ላይ ያለባትን ልጃገረድ ከብት የሚያግድ ሸውራራ ልጅ ይጠይቃታል

.. ለአፌ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል

484. ምስ ሚዝ ባወሽን ጉቱማ ሚኬ ጌስ

. እርቦ ላም የሌለው ደረቅ አልበላም ይላል

.. አቅሙን አያውቅ

485. ምስ ሚዝያ ሀይቅን ሄዘንቶይ ጨዬታ ኤኬስ

. እርቦ ላም ብትሞት በሶስተኛው ሰው ላይ ለቅሶ ይደረስበታል

.. አንዱ ሊበላ አንዱ ገገባ

486. ምስ ሚዝዮ ኡዱፑን አግና ኡይን ጭም በው ሜቶቶ

. የእርቦ ላም ወተት ዘጠኝ ወር ጠጥቼ ሽማግሌ ይቸገር

.. ባወጣ ያውጣ

.. ያበጠው ይፈንዳ

.. ይሉኝታና ጥቅም አብሮ አይሄድም

487. ምስ ሚዜ ጎደይ ኤሬተይ ጢሴ ጌስ

. የእርቦ ላም ጌታ ሙቁ ዱቄት ነው ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

488 ምሽረን ዼአይስ ገውሱ ሂለንችያ

. ጫጉላ ቤት ነኝ ትላለች ሸክላ ሰሪ

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

489. ምሽርያ ቀረ ግን እፍታ ግአውሱ

. ሴትየዋ አዋቂ ናት ሲሏት መዝጊያ ላይ ትንጠላጠላለች

.. አበጀች ቢሏት የቄሱ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

490. ምሽርያ አንቱኩሽን ብተኔ ግታ ብርሼስ

. ሴትየዋ ሳትፈቅድ ሰውየው ትጥቁን ይፈታል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

491. ምሽርያ አተ ጥለይስ ጋደ ግያፔ ሱቄነን ክየውሱ

. ሴትየዋ በጣም ንፁህ ልሁን ብላ ከገበያ ሳትፈሳ ትወጣለች

.. እጅግ ስለት ይቀዳል እፎት

492. ምሽርያ አዱዋ አይቀደ ሉሆ አቶ ሽመውሱ

. ሴትየዋ ወሬ ይዛ የተሸነቆረ እንስራ ትገዛለች

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

493. ምሽሬስ ግድን ግመነ ጊሽን ዎዴ ውሬስ

. ሴትየዋ በደንብ ስከብር እሾማለሁ ስትል ጊዜው ያልፍባታል

.. ጊዜ ወርቅ ነው፤ ግን ሃላፊ ነው

494. ምተን አውጌ ግቴ? አይ ቶኮ ግን ፐጠን መይዝድ ሀይቅን መይዝየ ፑቶይ ግተ ጌስ

. ከእንጨት ሁሉ ክቡር የቱ ነው? የቱን ልትክል ቢሉ በሕይወትም ሆነ በሞት ጊዜ የሚያለብስ ጥጥ ክቡር ነው ይሏል

.. ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት

495. ምተፔ ላፍ ብስ አስፔ ላፍ ምርዶ

. ከእንጪት ትንሽ ‹ብሳ› ከሰው ትንሽ ሀሰተኛ

.. አባይና ስንቅ እያደር ይቀላል

496. ምታ ከዎይ አይቤ ማን ፑቶ ጌስ

. የእንጪት ንጉስ ምንድነው ቢባል ጥጥ ነው አለ

.. ከእንጪት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት

497. ምችያ ምቼሶን ሚዝ ማጦሯ ገውሱ

. እህት እህት ቤት ከብት አይታለብ ትላለች

.. ምቀኛ አታሳጣኝ እንዲሉ

.. ጠላት ይወጣል ከቤት

.. የሰው ጠላቱ ከቤቱ

498. ምችያ ሚጭን እሸይ ዶሴነ

. እህት ስትስቅ ወንድም አይወድም

.. ታሞ ከመማቀቅ ይሻላል መጠንቀቅ

499. ምችያ በይነ ማየን ፐርሶይ ሳሜስ ጎፐ እሽ በያነ አለን ጉዬ ጤሎፐ

. እህት በሌለችበት ገበያ ጠላ ጠማኝ አትበል ወንድም በሌለበት ጦር ሚዳ ወደ ኋላ አትይ

.. ዘመድና መድሃኒት የተቸገሩ ዕለት

.. ወንድም ለማርማርታ፡ ጋሻ ለመከታ

500. ምችያ ዱርሰ ሞርን እሸይ ዩለቴስ

. እህት ጭፈራ ብታበላሽ ወንድም ያፍራል

.. አብ ሲነካ ወልድ ይነካል

501. ምኑዋ ምኑዋ አገኔ ሹጉዋ ሹጉዋ ምረኔ

. ጉበዝ ጉበዝ ሊተው ሰነፍ ሰነፉ ሊገደል (ጉበዝ ጉበዝ ሊተው ደካማ ደካማው ሊገደል)

.. የምታሸንፈውን ምታ ቢሉት ወደ ሚስቱ ሮጠ

.. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

502. ምኖይ ምን አድድ ምተን አቴስ
. በጣም ከማየሉ የተነሳ ዱር ያድራል
.. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ አመልማሎ ይስጡት ይፍተል እንደናቱ

503. ምኪኩዋ ደሮይ ሺምፑዋ ቡርቅሲስ
. እንቅስቃሴ ሲበዛ ወለምታ ያመጣል
.. እጅግ ስለት ይቀዳል እሬት
እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት

504. ምጥ ኢሂድ ጡጌቲ? ጤስ ኤሂድ ሜቴቲ?
. ለቅሞ አምጥቶ ይቃጠልበታል? ጠርቶ አምጥቶ ይበላል?
.. በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ
.. ባጐረስኩ እጄን ተነከስኩ

505. ሚሽይኔ ጭመይኔ ስጌቴስ
. ገንዘብና ሽማግሌ ያስታርቃል
.. ገንዘብ የደም ስር

506. ሚኪ ጊደ ኤያ ሚዘይ ቶእን ቤአ
. አልበላም ያለውን ሞኝ ላም ስትነጥፍ ታያለህ
.. ለመታዘብ ያብቃህ

507. ሚዘይ ሃተው ቢን ሀሬ ማልዱወው አቴስ
. ላሞች ወደ ውሃ ሲሄዱ አህያ ከማሽላ አገዳ ውስጥ ይቀራል
.. ሆዱን የወደደ ማእረጉን ይጠላል

508. ሚዛ ሀሬነ ጋሞይ አሾቼ ሀሬ ሚኪ ጊስ
. ከብት የማያረባ አንበሳ ያለስጋ አልበላም ይላል
.. የምታጠልቀው የሌላት የምትከናነበው አማረች

509. ሚዛ ሜቂተይ አልን ቢድ ቃጭያጋ ገልበን ዎዷስ
. የላም አጥንት ሲወረውሩት ሄዶ ፋቂ በሚፍቅበት ቆዳ ላይ ይወድቃል

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

.. ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ

510. ሚዛ ጭማ ጨይን አሳ ጭመይ ዬኬስ

. የከብት ሽማግሌ ቢረግሙ የሰው ሽማግሌ ያለቅሳል

.. ነግ በኔ

.. አብ ሲነካ ወልድ ይነካል

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

511. ሚዛፔ ሲንተው አድዳጌ ጋሙዋሰ ጉዬ አትዳጌከ ጋሙዋሰ

. ከከብቶች ወደ ፊት የቀደመም ወደ ኋላ የቀረም ለአንበሳ ሲሳይ ይሆናል

.. ከባልንጀሮቿ ከፍ ያለች ማሽላ ለወፍ ወይም ለወንጭፍ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

512. ሚዝያ ሞዳሱ ጋደ ሹኮፐ፣ ሹካርገደ ሜቶቶፐ

. ላሜ ሰባች ብለህ አትረድ፣ ካረድክ በኋላ እንዳትቸገር

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

513. ሚዝያ በ መልኡወው ብረሰደ አወ ማደውሱ

. ላም ለራሷ ፍላጐት ስትል ተጠቅታ ባለቤቷን ትጠቅማለች

.. ዳን ያለው መድሃኒት አለው

514. ሚዝያ እስኖሽን ናቶ ሚዛ ጨከ ጨከ ላግቴ ጌቴስ

. ላምዋ አንድ ሆና ልጆች ላሞቹን እያከፋፈላችሁ ንዱ ይኋል

.. ለእብለት ስር የለው ለእባብ እግር የለው

.. ሞኝ አይታወቅብኝ ባይ

.. አስመሳይ

515. ሚዝያ እስኖሽን ናቶ ሜህያ ሻከ ሻከ ላግቴ ጌስ

. ላሚቷ አንድ ናት ግን ከብቶቹን ለያይታችሁ ንዱ ይላል

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

516. ሚዳኔ ቢዳጋ ገኪስ

. የበላ የሄደውን ይደርስበታል

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

.. የበላ ቢያብል ገላው ይናገር

517. ሚዶ ምቴኮ ገክድ ቦለው ጤሌቴስ

. ከበሉበት ዛፍ ሲደርሱ ወደ ላይ ያንጋጥጣሉ

. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

518. ሚዶበን አይሰይ መልኦ አሾይ መልኦ ማን ጠይ ክችያጌ አይሲ ሚዶበን ነዎስ ማልኦ

. ከሚበላ ነገር ቅቤ ይጣፍጣል ወይስ ስጋ ቢሉ ሁለቱም ያልቃሉ ምን ያረጋል ከሚበሉት ነገር በረሃብ ጊዜ የሚበላ ነገር ይጣፍጣል።

.. የሚጣፍጥ ምግብ ሲርብ የበሉት ነው

519. ሚጬሽን ሃተይ ከና ሚኤስ

. እየሳቁ ውሃ ውሻን ይበላል

.. ቀልድና ቅዘን ቤት ያበላሻል

.. ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው

520. ሚጬየ ጌለእዮኔ፡ ቀጥየ ዱሩማኔ ጊዳ

. ሳቂታ ልጃገረድና የሚያደናቅፍ ጉቶ እንዲሉ

.. በማር የተሸፈነ መርዝ

.. የጭቃ እሾህ

521. ሚጪኮነከናስ አቻ ቦታ እሚስ ዶፌቴነኩቶስ አይፌ ቦኡዋ እሜስ

. ለማይስቅ ውሻ ነጭ ጥርስ ለማይገላምጥ ዶሮ ቀይ ዓይን ይሰጠዋል

.. ነገር ያለቦታው

.. ቆሎ ለዘር እንዶድ ለድግር አይሆንም

522. ሜህያ ሀሮይ ሞቶስኔ ሞኅስኔ

. ከብት ማርባት ለሙግትና ለቀብር

.. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

.. ገንዘብ የልብ ስር ነው

523. ሜህያ ሱተይ አሰን ገኪስ፣ አሳ ሱተይ ቢተን ጐጌስ

. የከብት ደም በሰው ላይ ይፈሳል፣ የሰው ደም መሬት ላይ ይፈሳል

.. ከብት ቢወፍር ለልደት ሰው ቢወፍር ለመሬት

.. ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት

524. ሜህያ ኦቶሮይ አው ገቲ ጌስ ኀደሬ

. ከብትን ኩራት የት ያደርሰዋል አለ ጅብ

.. አያ ጅቦ ሳታመሀኝ ብላኝ እንዲሉ

525. ሜለ ሜቅ ሜቆፐ፣ ሜጨዑተ ሺቀደ ተነ ቤአ ገውሱ እትምያ

. ገዞም ብለሽ ቂን ቂን አትበይ፣ ታጥበሽ ቀርበሽ እይኝ ትላለች ቡላ

.. የኔን ወጥ በቀመስሺው ያንቺን በተውሽው

.. የሰው ልክ አለማወቅ

.. ሙያ በልብ

526. ሜለ አቀነ ዎንጠፊይ ተመ አቾን ኤቂስ

. ጠሙን የሚያድር ብልት (የወንድ) እሳት ዳር ይቆማል

.. ምኞት ያከሳል

.. የቾኮለች አፍሳ ለቀመች

.. የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል

527. ሜለ አይሰነው ኤቀደ ተ ኔው ጋሼ ኡክያኮ ኢቴ ገውሱ

. ጠም ልታሳድር አስባ ጤፍ ቂጣ ብጋግርልህ ይከፋሃል ወይ ትላለች

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው

528. ሜለነ ሃተይ ከና ሜስ

. የሚደርቅ ውሃ ውሻ ይበላል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው

529. ሜረ ሎእያ አይሰ ውቂተው ኢተ

. መልከ ቀና ቅቤ በመስረቅ አደገኛ ናት

.. የሰው ክብሩ ግብሩ (ተግባሩ)

.. ሰው መሳይ በሸንጎ

530. ሜረ ኤሬናሮ ሀች ምኪከነ ገውሱ ምሽርያ

. ጭራሽ አርጊ የማላውቀውን ዛሬ ላንቋልጥ ትላለች ሴትየዋ

.. ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

531. ሜረይ ዎርን ኦርጌ ሴሴስ

. መልኳ ሲጠፋ (የወጣትነት ዘመኗ ሲያልፍ) ወጠጤ ይኮራባታል

.. ካረጁ አይበጁ

.. ልጅነት ተመልሶ አይመጣም

532. ሜርኩዋ ኬታ ኮይሽን ሼምፑዋ ኬተይ ክዬስ

. የብጉንጅ ሰንኮፍ ለማውጣት ሲሉ ነፍስ ይወጣል

.. አሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል፤ የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

533. ሜሬታ መቆይ ዛሬነ

. ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

.. ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

.. ይታደሗል እንጂ አይታገሉም

534. ሜቅ ኤርዳጌ ዶግ ኤሬስ

. ተሰብሮ የለመደ ማንከስ ይችልበታል

.. የደረሰበት ያውቃል

.. ላይችል አይሰጠው

535. ሚቄተይ ምንኮ አቻ ሜንቴስ፣ አቸይ ምንኮ ሜቄታ ሜንቴስ

. አጥንት ከጠነከረ ጥርስ ይስበር፣ ጥርስ ከጠነከረ አጥንት ይስበር

.. ከበሬታ ከራሱ የሰነፈ ከዋሱ

.. የቻለ ያንሳሽ

536. ሜቄተይ ሜቶ አንሰይ አጮ

. አጥንት ችግር ነው ሀብታምነትም እዳ ነው

.. ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች

537. ሜቱወው ግጦ ቦጌ ዎድራ በቅ ኦይቁስ

. ለችግር የታጠቁት ቁምጣ ከጭን ጋር ይያያዛል (ይጣበቃል)

.. ችግር ነው ጌትነት

.. የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

538. ሜቱዋዮ ቱቄ ዎሬስ

. የተቸገረች ሴት በወጋግራ ተገጭታ ትሞታለች

.. በወደቀ ዛፍ ላይ ምሳር ይበዛበታል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

539. ሜትን ኩቱወን ጫናስ ግን እንከ ተው ድድ ጋየርኪ ጌስ

. ተቸግሬ በዶሮ ጫንኩ ቢል በሷ ላይ አላል አስቀምጥልኝ አለ ይባላል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

.. የለማኝ ለማኝ ቁርንጮዩን ቀማኝ

540. ሜቴቲ! ጌስ ቦጋል

. ሊበላ ነው! አለ ቦጋለ

.. ሞኝህን ፈልግ እንዲሉ

541. ሜቴነ ሜኒትያ ዘዘሬ ኪቴተውሱ

. ያልቸገረት ሚዜ ወንፊት ትላለክለች

.. ባለቤቱ የጠላውን አሞሌ ባለዳ አይቀበልም

542. ሜቴነይ መስቀለ ዬተ

. የማይቸግር የመስቀል ዘፈን ነው

.. ወይ ጉዴ ላግባሽ አለኝ ነጋዴ

.. አዋጅን በጆሮ

.. ያደባባይ ምስጢር

543. ሜቶት አይፍያ ቱገቶይ አይቂስ

. የሜቶትን ዓይን ቱገቶ ያይዛል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

.. እውር እውርን ይመራል

544. ሜቶትደ ጢሌ ጨርኩዋኮ ሺቂስ

. የተቸገረ ዱቄት ወደንፋስ ይጠጋል

.. የተቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

.. የቸገረው እርጉዝ ያገባል

545. ሜቶትደይ ዎዳ ኤኪስ ዬልን አፉዋ ቢስ

. የተቸገረ ባተሌ እርጉዝ ያገባል ስትወልድ ገደል ይገባል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

.. የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

546. ሜቶትዳጌ ሀርያረ ዝንኤስ

. የተቸገረ ከአህያ ጋር ይተኛል

.. የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

547. ሜቶትዳጌ ሻሃርዮ ኤኬስ

. የተቸገረ ነፍስጡር ያገባል

.. የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል

.. የቸገረው እርጉዝ ያገባል

548. ሜቶትድ ኡክዶ አይታ ሀን ኦት ሰጤስ

. ተቸግረው የጋገሩትን ቂጣ በአፍ ሙሉ ይገምጣል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. ያልተነካ ግልግል ያውቃል

549. ሜቶይ በይነ ሜንትያ ከዎ ሸንከን ሀይቀውሱ

. ያልቸገራት ጉሽ በንጉስ አደን ትሞታለች

.. ሳይቸግር ጤፍ ብድር

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትመጣለች

550. ሜቶይ በይነ ከንያ ግያ በውሱ

. ያልቸገራት ውሻ ገበያ ትሄዳለች

.. ውሻ ሳይቸግረው ገበያ ወጥቶ ይደበደባል

551. ሜቶይ በይነ ጎሸንቸይ ሰነየን ሀይቁስ

. ያልቸገረው ገበሬ በሰኔ ይሞታል

.. ስራ ያጣ ገበሬ በሰኔ ይሞታል

.. ስራ ያጣ ለማኝ አፍሶ ይለቅማል

552. ሜቶይ አይቅዶጋ ሀርጌከ ተ ገከናሸን ዬዶፐ ጌስ

. ችግር ያለበትን በሽታም ደረስኩ አትልቀቀው ይላል

.. በቦሃ ላይ ቆረቆር

.. በወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል

553. ሜን ቁመይ ሰዎ ኢተ

. የማይበሉት ምግብ ይሸታል

.. ምኞት ያከሳል

554. ሜነ ቁመይ ቢተ ኡባ ሰዌስ

. የማይበሉት ምግብ አገር ሁሉ ይሸታል

.. ላም አለች በሰማይ ወተቷንም አላይ

555. ሜነ ኔዋነ በስማም ሜቴቴነን ዪዳ ተ አዋኔ በስማም

. መጥኔ! ሳይበላ ለመጣ አባትህ፣ መጥኔ ሳይበላ ለመጣ አባቴ

.. እባብ ለእባብ ይተያያሉ ካብ ለካብ

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ

556. ሜንተርሻ ጣልያ ዎዴ ቀንጡዋፔ ቦርሶይ ኢተ

. በጣሊያን ጊዜ ከንፈር ከመቆረጡ ማስቀየሙ ይብሳል

.. የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

557. ሜእ ኤረይ ዎብ ኤሬስ ጌቴስ

. መሰበር የሚያውቅ ማንከስ ያውቅበታል አሉ

.. እንዳገሩ ይኑሩ እንደወንዙ ይሻገሩ

.. ላይችል አይሰጥም ላይጠግን አይሰብርም

558. ሜዜ ኦላ ኦሌስ

. ልምድ (ብልሃት) ውጊያ ይዋጋል

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ ማለቅ

.. ልማደኛ አይጥ ፈረስ ትቀድማለች

559. ሜድያጋ ነአ ጩቸይ ሜስ

. የላጭን ልጅ ቅማል በላው

.. ያባይን ልጅ ውሃ ጠማው

.. የላጭን ልጅ ቅማል በላው

560. ሜድርስ ዙቁርሰ ኤክን ከፎ ኡበው ዞኮይ ዱጨስ

. ሜፁርሳ የተባለ ወፍ ትል ቢያነሳ የወፍ ሁሉ ጆርባ ይበጠሳል

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

561. ሞር ናት ውርን ተ አይ ጌለኔ ገውሱ

. የሞሪ ልጆች በሙሉ ካገቡ እኔ ማንን አገባለሁ ትላለች

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

562. ሞርክያ ኢተይ ስገ መለ

. የቂም መጥፎ ፍቅር (እርቅ) የሚመስል

.. የታወቀ ጠላት ከወዳጅ ይቆጠራል

.. የጨዋ ልጅ ሲፋታ የተጋባ ይመስላል

563. ሞቶይ ኦሶ ግዴነ

. ሙግት ስራ አይደለም

.. ሰርቼ ልብላ ከለምኜ ልብላ ይሻላል

.. ነገር አለኝ ከማለት ስራ አለኝ ማለት ይሻላል

564. ሞይስ የሼኔን ዱፉወ አተ ጌቴስ

. ከሸኘሽኝ ላይቀር መቃብሩን አሳልፊኝ ይላል

.. ከለገሱ አይቀር ይንጋለሉ

565. ሞይሲድ አወ ሜሌቴሽን ጠሚድ ዎድ ነአ ክዩስ

. ሲሸኝ (ሲያጅብ) አባት የሚመስል ሲጠባ ተመልሶ ልጅ ይመስላል

.. ትፈጭ የነበረች ማንጓለል አቃታት

566. ሞይሶ ግን ዟንአነ ጌስ

. ልሸኝህ ያሉት መኻታ (አልጋ) ይላል

.. የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ያድርቅ

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

567. ሞዴነ ሞሆይ ሱሌነን ፔንቴስ

. ያላፈሩት ሰባራ ሳይጥዱት ይፈላል

.. ተውሰው ያመጡት ሰባራ ሽክላ ሳይጥዱት ይፈላል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

.. በቦሃ ላይ ቆረቆር

.. የባሰ አታምጣ

568. ሞዶ ዶርሰይ ዶምኤስ

. ያረቡት በግ መልሶ ይዋጋል

.. ባጕረስኩ እጄን ተነከስኩ

569. ሞደነው ምን ሞገነው ገቴስ

. ለመወፈር የበሉት ለሞት ያበቃል

. ለመወፈር የተበላው ለመቃብር ያደርሳል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. ማር ሲበዛ ይመራል

570. ሞዱወውኔ ሞይትልያስኔ ዎዘን ባወ

. ወፍራምና ሃእረሞት ልብ የላቸውም

.. ከወፈሩ ሰው አይፈሩ

571. ሞዶይ ግልቀናሽን ግልቀይ ሀይቁስ

. ወፍራም እስቲከሳ ከሲታ ይሞታል

.. ወፍራም ቢከሳ ይቀጥናል፣ ቀጭን ቢከሳ ይመነምናል

.. ሀብታም እስከሚራብ ድሃ ቀድሞ ይሞታል

572. ...ሞጋ አዳነው አቻ ጬደስ

. መንጃ የበላውን ለመናገር ሲፈልግ ጥርሱን በስንጥር ይወጋል

.. ውሻ ሆድ ውስጥ ቅቤ አያድርም

# ሰ

573. ሰሉወን መይራመ ሰንቃ ዶይን፡ ሰአን ዴእየ ኩቶይ ዎንታ ኤሬሰ
. ሰማይ ቤት ማርያም መዝጊያ ብትከፍት መሬት ያለው ዶሮ መንጋቱን ያውቃል
.. እግዜር የሰጠውን ሰው አይከለክልም
.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

574. ሰሉዋ ባነ ተ ዴእሽን ሸበ ባነ ኔ ዬከይ ገውሱ ሂለንችያ
. ሰማይ የምሄድ እኔ እያለሁ ሻባ የምትሄድ አንተ ታለቅ ሳለህ አለች
.. እናቱ ገበያ የሄደችበትም የሞተችበትም እኩል ያለቅሳሉ
.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

575. ሰሉዋ ባናጌ ዲሽን ቦረው ባናጌ ኤሶቴሰ
. የሞተውን ትቶ በሬ ጠምዶ ለማረስ ይቸኩላል
.. ከራስ በላይ ንፋስ
.. ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ

576. ሰልጉይ ሰሬታ ማነ ግን ሰልጎ ኣይያ ሰሬታ ሚኬ ገውሱ
. ሳልጉ (ስም) ቅይጥ እበላለሁ ሲል እናት ቅጥይ አልበላም ትላለች
.. ሆድ ድንጋይ እበላለሁ ቢል ጥርስ ከማን ጋር ተማክረህ አለው ይባላል

577. ሰሌነይ በይናረ እርፐኔ ቁምኤስ ገውሱ
. ሰሌን የሌላት ቁርበት ይቆረቁራል ትላለች
.. አህያ የሌለው ፈረስ ይንቃል

578. ሰሎይ ጎዩቴ? ኣው ቀንጌቴ?
. ሰማይ ይታረሳል ወይ? አባት ይረገማል ወይ?
.. የአባት ባለጌ የበርኖስ አሮጌ የለም

579. ሰሬታ ሰንታረ ጭመደ ምተ

. የተደባለቀን (ቅይጥ) በጐመን አታለህ ዋጥ

.. ኮሶን በማር

580. ሰሮ ዴእየ ሸሎይ ብቸርያ ኩትዮ ሸሜስ

. ደህና የተቀመጠው ገንዘብ ቀኝ ቃገር ዶሮ ይገዛል

.. ጥፋ ያለው ከመቀነት ወጥቶ ይጠፋል

581. ሰሮ ጌነን ሰተሯ ዴንድየ ኤቀ አቻ

. ሰላም ሳይል ለመንከስ የሚነሳ ገጣጣ ጥርስ

.. አይን ካላየ ግንባር

582. ሰሮተይ ጨዩታ ኤሄስ

. ሰላምታ ሲበዛ መርዶ ያሰማል

.. አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል

583. ሰባኬ ሰንተይ ሰይኖ ዎትን መስቀይኖ ከኤስ

. የቀባጭ ጎመን ሰኞ ተጥዶ ማክሰኞ ይበስላል

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

584. ሰብ ሳሎ ኪስን ምሸርያ ኡዱለ ምተን ጨዲያ ከተውሱ

. ያሞገሷት (በጣም የካቧት) ሴት በዘነዘና የጐደሬ ምግብ ትቀጠቅጣለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መፅሐፍ አጠበች

585. ሰብዶ ሰከካ፣ ኡስትዶ ዬሶ ማታ

. ያሞገሱት ቆንጆ የሚያምገው ትኩስ ወተት

.. እንከን የለሽ

586. ሰብዶ ናአ መችያ ቦይና ሞሁወን ከተውሱ

. ያሞገሷት የልጅ ሚስት ጎደሬ በሰባራ እንስራ ትቀቅላለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

587. ሰተው አዘሌ፣ ቁመው አጎሮ

. ለመንከስ ሰነፍ – ለምግብ ስልቻ

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

588. ሰንተን ሰንጋ ሽምየ አጎ ያረቴ

. ጕመን ሽጣ ሰንጋ የምትገዛ የአጕ ልጅ ያሬቴ

.. ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም

589. ሰንታ ሚደ ዎልቀይ ፑዴታ ክዩነ

. ጕመን የተመገበ ጉልበት ዳገት አይወጣም

.. ሆድን በጕመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል

590. ሰንታ ከቴናረ ቡስኩቴ ቀዩ ገውሱ

. ጕመን የማትቀቅል ብስኩት ጥሬ ነው ትላለች

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

.. ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ግን ይደናገር

591. ሰንታ ጠውሄናረ ቡራቶይ ሀርቆ ገውሱ

. ጕመን የማትቀነጥስ ጭኮ እብቅ ነው ትላለች

.. ለአህያ ማር አይጥማትም

.. ይሉኝን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ

592. ሰንታ ፕላረ ምን ሎቆዩስ

. ጕመን በአይብ ቢበሉት ያቅለሸልሻል

.. ለአህያ ማርት አይጥማትም

593. ሰንገ ፕረይ ሰንታ ሜነ

. ሰንጋ ፈረስ ጕመን አይበላም

.. ስም ይበልጣል ከስር

594. ሰአ ከስቶሌ ዴእሽን ሰሮ በለይ በቁቴስ

. የነከሰው ቁንጫ እያለ ደህና ገላ በጥፊ ይመታል

.. አይጥ በበላበት ዳዋ ተመታ

595. ሰአሮ መጠነ ጊሸን እድመይ ላሌቴስ

. የመሬቱን እለቅማለሁ ስትል የእቅፏ ይበተናል

.. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

596. ሰአ ኦቴነይ ምታ ጨራ ከዩስ

. መሬት የማያርስ እንጨት ጫፍ ላይ ይወጣል

.. የማያጠገብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

597. ሰአን ግዴናጌ አርሰው ጎቺስ

. መሬት ላይ የማያረካ (የማያጠግብ) ወደ አልጋው ይጐትታል

.. ላያረካኝ ቂጤን አረጠበኝ

598. ሰአይ ሰሬነሸን ሳኣጋ ኤኬስ

. መሬቱ ሳይደልብ የመሬቱን ይወስዳል

.. አይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች

599. ሰአይ ባስ ቀምድ አሰ የሼስ

. ጊዜ ለራሱ መሽቶ ሰውን ያስፈራል

.. ያልበሉት እዳ ያልጠሩት እንግዳ

600 ሰአይ እጥን ሻሬቾይ ዴሻ ሜስ

. ኑሮ አልመች ሲል ቃልቻ ፍየል ይበላል

.. የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

601. ሰኣጋ ቆርሸን ክይዋጌ ላሌቴስ

. የመሬቱን ስትለቅም የብብቷ ይወድቃል

.. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

602. ሰእያ ሰርቁኩሸን ሰንትያ ገዴን ኣተውሱ

. ዋናው የሚበላ ምግብ ሳይደርስ ጐመን ይለመልማል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

603. ሰውያ አንቱኩሽን ጎደይ ኢርቹዋ ሂጤስ

. ጋለሞታዋ ሳትፈቅድ ጌታው ነጠላ ያነጥፋል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጥ

604. ሰውያ ኢንደይ ቂምኤስ ገውሱ

. ጋለሞታዋ አልጋ ይቆረቁራል ትላለች

.. ለአህያ ማር አይጥማትም

605. ሰውያ ጌለ ግን ዩከውሱ

. ፊት አግቢ ቢሏት ታለቅሳለች

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

606. ሰዌስ ሙጃሎ ጫመ

. ለፊት ሙጄሌ ጫማዋ ነው

.. ሰነፍ ይዐድቃል ቢለው ገለባ ይበቅላል ወይ አለው

.. ሰነፍ በአል ያበዛል

607. ሰዌስ ሰንታ በእን ምዬ ጌሌስ

. ጋለሞታ ጉመን ብታዝል የጉድን አጥንቷ ይቀጫል

.. ሰነፍ ይዐድቃል ቢለው ገለባ ይበቅላል ወይ አለው

608. ሰዌን ሰንትዷ ጌለእዮ ኤኪቴስ

. በፊት እየተለማመዱ ፏጃገረድ ያገቧል

.. ጅብን ሲወጉ በአህያ ተከልሎ ነው

.. ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል

609. ሰዎቴት ሱቄተ ኤርሴስ

. ፊት መሆን ፊትል ያስተምራል

.. ችግር ብልሀትን ትፈጥራለች

610. ሰደልን ሰበክን አይፌ ቱኬ ገኬነ

. ቢደባልቁት ቢያግባቡት እውነተኛ ቡና አያክልም (አይሆንም)

.. በስም የተቀባ ጥርስ ቢስቁበትም አያደምቅ ቢበሉበትም አያደቅ

611. ሰጠን ኬጥዮጌኔ ሰእ ገንጥዮጌኔ እሱዋ

. በጥቀርሻ መስራትና ገምጦ መጐንጨት አንድ ናቸው

.. መሰረተ ጠንካራ

.. አስበው የሰሩት አልመው የወጉት

612. ሰጦረ ሰሬነይ ሰአሮ ተታፈስ

. የጐረሰው ሳይስማማው ሌላ ከመሬት ያነሳል

.. ከስስታም አንዱ ያንቀው አንዱ ይወድቀው

.. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

613. ሱረን ቀችዶ ፐረይ ዴእሽን ዛላን ቀችዶ ፐረይ ሞዴስ

. ሰርዶ ላይ የታሰረው ፈረስ እያለ አለት ላይ የታሰረው ፈረስ ይወፍራል

.. ሰው ካለው እግዜር ያለው ይበልጣል

614. ሱሬ ኤዝግኮ ሂተ ምዮ የሸስ

. በጣም ካሰቡበት የመኝታ ክፍል ያስፈራል

.. አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል

615. ሱቁዋስ ላፍየ ዱልያ ተመይ ሞ

. ለፈስ የሚያንስ ቂጥ እሳት ይብላው

.. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

616. ሱቆይ ሽየ ላዘንተ

. ፈስ የአር ዋዜማ ነው

.. የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው

617. ሱቆይ ታፔ ክይድ ጎዳ ሜንቶ ጌስ

. ፈስ ከኔ ወጥቶ ግድግዳ ይሰበር ይላል

.. ከራስ በላይ ንፋስ

618. ሱንተይ በይነ ከነይ ቲቶ ቲቶ ጊሽን ሀይቂስ

. ስም የሌለው ውሻ ቲቲ እየተባለ ይሞታል

.. ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች

619. ሱንታ ኬታይየ ሱሰን ግጠውሱ

. የሹም ሚስት በወፍቾ ትታጠቃለች

.. ንጉስ ቤት መርፌ ይቸግራል

620. ሱንደዶንተሶ ሱልእያ ሱጊንኔ ቃጡኩ ዬዲነኔ ምቹኩ

. የነሱንደዶ ቤት ሽልጦ ቢገፏትም አትነቃነቅ ቢረግጧትም አትፋጅ

.. የግመል ሽንት አይገማ አይሸት

.. የማይረባ ሰው ሞት መገላገያው ነው።

621. ሱኩልአይ በር ቁና ፐትቤነሽን በር ቦሉወው ጠልያ ዱቴስ

. ጅግራ የራሱን ጉባጣ ሳያቀና ለአማቹ መድሃኒት ይቆርጣል

.. መርፌ የራሱን ቀዳዳ ሳይሸፍን የሌላውን ይደፍናል

622. ስልኬ ዮሁዋ ዮቴስ፤ ስኔ ቱክያ መኪስ

. ስልክ ወሬ ያወራል፤ ስኒ ቡና ይሰፍራል

.. ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል

623. ስመነው ቤሌኮፐ፣ ስእሰነው ሙነቆፐ

. ለመመለስ አትኩብልዬ፣ ለማበላሸት አታቡኪ

.. ትዝብት ነው ትርፉ

.. የማይሆን ነገር ለባልሽ አትናገሪ

624. ስርየ አገዞይ ቴጉልሳ ዩድድ ጤሌስ

. ተጠራጣሪ ባል ጉልቻ ረግጦ ያያል

.. የማይተማመኑ ጓደኞች በየወንዙ ይማማላሉ

625. ስንተ አቸይ ሰተ ኤሬሽን ጮንቸ ኤሬነ

. የፊት ጥርስ መንጪት እንጂ ማኘክ አይችልም

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

.. እዩኝ እዩኝ ያለች ደብቁኝ ደብቁኝ ትላለች

626. ስንተ ጤራ.ጋ ቶረይ ጨድን ግዱወጌ ዳፉርን ጉዬ ገጣጌ ኩንዴስ

. ከፊት ጫፉን በጦር ቢወጋው የመካከለኛው ሲደክም ከኋላ ዳር ያለው ይሞታል

.. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

627. ስንተት ሀይቅደ ኡረይ ዱፎ ኪሀ ኤኪስ

. ቀድሞ የሞተ ደህና መቃብር ያገኛል

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

.. ያመነታ ተመታ

628. ስንግዶበን ሎሜ ሰዎ ሽቶይ ሰዎ? ግን አት ክችያበ ግዴኔ ስንግዶበን ነእ ሰዎ ጌስ

. ከሚሸትት ነገር ሎሚ ይሸታል ወይስ ሽቶ ቢል ሁሉም ቀሪ ነው ከሚሸትት ነገር ልጅ ይሸታል ይላል።

.. ልጅ ጠልቶ ምን ይወደል ማር ሸጦ ምን ይገዟል

629. ስዬነ ሀይተይ ሾሮረ ኦሼስ

. ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ጋር ያጣላል

.. ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ያጣላል

.. በማታውቀው እጅህን አታድርሰው

630. ሲርያ ዜኡዋ ነእዮ አቻ ዜኡዋ ነአይ ኦይቼስ

. የአፍንጫ ግምን ልጅ የጥርስ ብልዝ ልጅ ያጫታል

.. ለአፊ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

631. ሲርያ ዴችን አይፌ ዬኪስ

. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

.. አብ ሲነካ ወልድ ይነካል

632. ሲሬ በይነ ጉዱንተይ አይፌ በይነ አዱዋ ኡዬስ

. አፍንጫ የሌለው አሳማ አይን የሌለውን (ቦሌ) ሆራ ይጠጣል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

.. ሰው ቢጤውን አያጣም

633. ሲድ ሲድ ሲቄተይ ስት ግ አቴስ

. እፍ እፍ ብለው የተፋቀሩት ተቆራርጠው ይቀራሉ

.. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

634. ሲቆ አሳ ቀጠይ ዱቴስ

. ፍቅረኞችን ስብቀት ይለያያቸዋል

.. ወሬ መጫኛ ይበጥሳል

635. ሴረ ገወራ ገውሱ ገባቦ ሶ ኤጩርያ

. የተከለከለ ድመት ትላለች የገባቦ ቤት አይጥ

.. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

636. ሴረይ በይነ ኩቶይ ኦላ ቤስ ጌቴስ

. ያልተቀጣ ዶሮ ጦር ሜዳ ይሄዳል ይባላል

.. ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ

637. ሴረይ በይነ ኬተን ከነይ አሳረ ሜስ

. ስርአት በሌለበት ቤት ውሻ ከሰው ጋር ይበላል

.. የእንደሻው ቤተ ክርስቲያን ተበልቶ ይቀደስበታል

638. ሴረይ በይነ ኬተን ፐረይ ኮራረ ጌሌስ

. ስርአት በሌለበት ቤት ፈረስ ከነኮርቻው ይገባል

.. የእንዳሻው ቤተ ክርስቲያን ተበልቶ ይቀደስበታል

639. ሴረይ በይነባ ሣድያኮ ቤጥያ ኪሰደ ቤሰርክነ ጌስ ከይሶይ

. ህግ ባይኖር ኖሮ ጠገራውን አውጥቼ ባሳየሁ ይላል ሌባ

.. የሞተ ልጅ አንገቱ ረዥም ነው

640. ሴር በይነ ሀሬ ግያን ዎንጠፋ ኪሴስ

. ያልተቀጣ አህያ ገበያ ውስጥ ቁላውን ያወጣል

.. ባለጌ ሲቀመጥ ቂጡን ገልቦ ነው

.. ባለጌን ካሳደገ የገደለ ዐደቀ

641. ሴባወይ ቡቻወ ዩሌስ

. ሪዛም ፂማምን ይወልዳል

.. ያልዘሩት አይበቅልም

642. ሴተ ፔቴለ ዎደለይ ቦይና ክይየን ኮምፔስ

. ምንም የሌለው ወንደላጤ ጒደሬ በኩበት ይጠብሳል

.. ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጐረቤቱ አይኖርም

643. ሶ በገይ ከውሸሽን ጠልያ ኡይድ ወልቀቀቴስ

. ከቤት በኩል ምንም ነገር የለውም ግን ኰሶ ጠጥቶ ይንጠባረራል

.. ቢከፍቱት ተልባ

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

644. ሶ አሶ ግን ዩለ ዝንኣስ ገውሱ

. እዚህ ቤት ቢል ወልጄ ተኝቼአለሁ አለች

.. ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት

.. ፍየሏ ወዲህ ቀዝምዝም ወዲያ

645. ሶ ኦለተይ ከበሽን ከሬ ኦለተይ ከሌስ

. እቤት ያለው ምስጥ ሲራብ የውጪው ይጠግባል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳትደፍን ለብዙ ሰው ትጠቅማለች

646. ሶሄነን ምየ ጌሌሾይ ቁፊድ አቂስ

. ሳያሽ የበላ ዝንኸሮ ሲስል ያድራል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

647. ሶሎይ ሰሉዋደን ሃክን አሸከረይ፣ ሻራደን ቆምን ግዱወን

ሺምፖ ገምአደ ዴአ

. ከፍ ያለ እንጀራ ኖሮህ በአሽከር እንደጉም ታጅበህ ረዥም እድሜ ኑር

.. ከፍ ያለ እንጀራ ይስጥህ

.. መልካም ምኞት

648. ሶርፔል ዎልቃ ውርስን መኩር ጨሻ ኤኪስ

. ሶርፈላ በጨረሰው ጉልበት የመኩሪያ ዳገት ይረገማል

.. አሳማ በበላ ጉፍናኔን በዱላ

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

649. ሶን ማቶትን ግያ ቶኪቴስ

. እቤት ቢሰክር ወደገበያ ይሸከሙታል

.. የፈተኛው ያገሳታል በላይ በላይ ያጉርሳታል

650. ሶን በይናጌ ደጉወን ጤሰይ ዱጥን ገኔስ

. እቤት ምንም የሌለው ደቦ ቦታ ወገቡ እስኪበጠስ ይጨልጣል (ይጠጣል)

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ

651. ሶን ቱሪን ኔነ ገቶፖ

. እቤት ሲቸገር አያድርስህ

.. የተከፋ ተደፋ

652. ሶን ኪህዶረ ቦራረ በውሱ

. እቤት ደልቷት እያለ ሌላ ፍለጋ ትሄዳለች

.. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

653. ሶን ዘደሎይ ኡንኤነ ሚገዘዮ ሻፈን ቦጆይ አይቂስ

. እቤት ጋጥ የማይጠባትን ላም ወንዝ ዳር ያለው ገደል ይይዛታል

.. ወስፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም

654. ሶን ዴእየ አሽከረይ ሶ ጒድዮ ቃቀቴስ

. እቤት ያለ አሽከር እመቤቱን ይከጅላል

.. አብሮ መኖር ያናንቃል

.. ያሳደጉት ውሻ...

.. ሆድ የኔ ነው ሲባል ቁርጠት ሆኖ ይገላል

655. ሶን ፔእደ ሙቴፔ ሽሎተን ፔእደ ኡዱንጥያ አደውሱ

. እቤት ከዋለች ንብ አደባባይ የዋለች ዝንብ ትበልጣለች

.. ከሞት አንበሳ ያለ ውሻ

.. ከሞተ ንጉስ የቆመ ባላምባራስ

656. ሶንጋ እጥደይ ቱንገ ቤቴስ

. ሶንጋ አልሄድም ያለ አዲስ አበባ ይሄዳል

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

.. ቢለምኗት እምቢ ብላ ትለምናለች

657. ሶይ፤ ግን ሶሎለውሱ ሶለ ግን ኡከ መውሱ

. ቤት ስሪ (ትዳር ያዢ) ሲሏት ታለምጣለች እንጀራ ጋግሪ ሲሏት ቂጣ ጠፍጥፋ ትበላለች

.. ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው

658. ሶግደን ብረስደ ሚዝያ ቦግደን ዩለውሱ፣ ሰሌነን ሻረደ ቆነሸየን ዩለውሱ

. ሶጊዳ የተጠቃች ላም ቦጊዳ ትወልዳለች ሰሌን ላይ ያረገዘች ሴት ቅጠል ላይ ትወልዳለች

.. ልማድ ከልጓም ይስባል

.. እሳት ካየው ምን ለየው

659. ሶግደን ኡንጨይ ኀለትን ሶ ዛርድ መችዮ ዴሬቂስ

. ሶጊዳ ሆኖ ቆጮ ሲበላ ቂጣ ውስጥ ቃጫ አግኝቶ ወደ ቤቱ ዘወር ብሎ ሚስቱን ይገላምጣል

.. አመል ቤት አይጠብቅም

660. ሸልቆ ሸሃረይ አዬ ዬሁዋ ድጌስ

. የማይረባ እርግዝና የናት ለቅሶ ይከለክላል

.. የማይጠቅም (አይጠቅም) ጋሻ ቂጤን አስወጋ

.. የማያዘልቅ ፀሎት ለቅስፈት

661. ሸመ ሻቼናረ ጎለን ቁጩተውሱ

. ገዝታ ያላከረመች በቃሚ ትጠርጋለች

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

662. ሸምዮ ዎዴ ገኬነ ጥንግሌ ሹክዮ ዎዴ ገኬስ

. ሲገዛ ያልነበረ ጭልፊት ሲታረድ ይደርሳል

.. ለጌሾ ወቀጣ አንድም ሰው አልመጣ፣ በመጠጡ ጊዜ ከየጎሬው ወጣ

.. ማን ያቦካውን ማን ይጋግራል

.. ቱሪ ናፋ በስራ አትገኝ ከገበታ አትጠፋ

663. ሸረሮቴ ተካሮ ኩሜነሸን ባፔ አድየ ላፑን ወረ ኬታ ደዴስ

. ሸረሪት አንድ ስንዝር አይሞላ ከራሱ የሚበልጥ ሰባት ክንድ ቤት ይሰራል

.. የናቁት ያስረግዛል

.. ሙያ በልብ

664. ሸሬቾይ አሰባ ከዬስሽን በሶባ ኤሬነ

. ቃልቻ የሰውን ችግር ይፈታል የቤቱን ግን አያውቅም

.. ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. መርፌ የራሱን ቀዳዳ ሳታይ ለብዙ ሰው ትጠቅማለች

665. ሸሬቾይ ጠልያ ኡይን ማጋይ ጉሱወው ቤስ

. ቃልቻው ኮሶ ጠጥቶ ባለሚሉን ያስቀምጠዋል

.. ገበዙ ኮሶ ጠጥተው አቃቢቷን አሻራት

666. ሸንካ ፐረይ ዬዴትዮ ኀደሬ ሀርያ ውድያ ጤሊድ አዴስ

. የአደን ፈረስ የሚያባርረው ጅብ የአህያ መንጋ እያየ ያልፋል

.. ከራስ በላይ ንፋስ

.. መጀመሪያ መቀመጫዬን አለች እንሰሳይቱ (ዝንጀሮ)

667. ሸንደይ ጕርቃ ወዴስ፣ ሸመይ ከሬታ ዶሴስ

. ሻንዳው ጕሪቃን ይደበድባል ግገር ጥቁር ይወዳል

.. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል

668. ሸከላ ሸመደ የገኑዋ ዬደውሱ

. የጭንቅላት ስጋ ገዝታ ስጦታ ትልካለች

.. ስም ይበልጣል ከስር

.. የያዘውን የወረወረ ፈሪ አይባልም

.. ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች

669. ሸኩዋጋ ኮየይደ ሾዳጋ ላለውሱ

. የቆጡን ስትፈልግ የብብቷ ይበተናል

.. የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች

670. ሻለ ቀርያ ካሎ ዱረውሱ

. የሻላ ቀበሌ ጕበዝ ራቁቷን ትጨፍራለች

.. የጠገበ እንደሚራብ አያውቅም

.. የጠገበ ራሱን አያውቅም

671. ሻም ኤሆ ቦይያ ምስ ኤሆ ስንተ አይፌ ሞሬስ

. ተገዝቶ የመጣን (ቦዬ) ምግብን ተለምኖ የመጣ የጕመን ዘር ያበላሸዋል

.. አተርፍ ባይ አጕዳይ

.. ሲጋጌጡ ይመላለጡ

.. አልጠግብ ባይ...

.. ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ·ተምራ ትመጣለች

672. ሻሻ ም አቀናፔ ሜለ አቀነ ጌስ

. ቆሎ በልቶ ከማደር ጦም አድራለሁ ይላል

.. አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ ጦም አድሮ ጥሩ መሸመት

.. ከእጅ አይሻል ዶማ

673. ሻሽ ሼሻ ከሎይ በኤነ

. የሻሼን ዝርያ ጥጋብ አይቀናውም

.. የሻሼ ዝርያ ጥጋብ አይችልም

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

674. ሻትየን ከትን ነአው አሼነ ውይናነ ጭመው

. በጣባ ተሰርቶ ለልጅ የማያተርፍ ስግብግብ ሽማግሌ

.. ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ

.. ይሉ አይሉ የታለ ቅሉ

675. ሻይ ጎሮሞቴ ኢናረ ጎሮሞትያ ማነው በምበርያ ዳጨስ

. የሻያ አገር ቡዳ የህናራን አገር ቡዳ ለመብላት በርበሬ ይድጣል (ይፈጫል)

.. እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ

676. ሻይ ጎሮሞቴ እናረ ጎሮሞትያ ሻይ ሜስ

. የሻያ ቡዳ የኢናራን ቆልቶ ይበላል

.. እሾህን በእሾህ

.. ቡዳ ቤት ሰላቢ ገባ

677. ሻይን እጥደ ባቄልያ ኮክን ጡቀውሱ

. ቢቆሏት እንቢ ያለች ባቄላ ስትቀቀል ትንጣጣለች

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

.. ለሁሉም ጊዜ አለ

678. ሻፋ ጨርያ ዬድን ሾድየው ሆኮይ ዱጤስ

. ጨፌ ቢረግጡ የእንቁራሪት ጀርባ ይበጠሳል

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

679. ሹሙራኮይ ሹሜ ግዶን ኡቲድ ሹሜ ዎደሮ ዶቂስ

. ስንዝሮ እንጉዳይ መሐል ተቀምጦ የእንጉዳይ ገመድ ይገምዳል

.. የአይጥ ምስክር ዲምቢጥ

680. ሹቸው የይድ ሹችያ ጨዴስ

. ለድንጋይ ፈርቶ ዳሌ ይወጋል

.. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

681. ሹክን ሹከና ጠይን መንጥ በይነን ዮፐ

. ቢታረድ ባይታረድ ያለ «ማንጣ» እንዳትመጣ

.. አደራ ጥብቅ ሰማይ ሩቅ

.. የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው

682. ሹክዮጌ አላዴ፣ በርስዮጌ ብረዴ

. የሚያርደው አላድ የሚያጉርሰው ጣት

.. ምን ያመጣ ድሀ ምን ያገሳ ውሃ

.. ላይጠቅመኝ ጭኔን አረጠበኝ

683. ሹግያሳ ደንቆይ ሰጤስ

. ለስላሳውን ገላ መኻገር ይነክሳል

.. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

684. ሽሎተን ፔእደ አሽከረይ ቢድ ጎዳ ኪቴስ

. ችሎት የዋለ አሽከር ሄዶ ጌታውን ያዛል

.. ቀን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል

.. መንደር ከዋለች ንብ አደባባይ የዋለች ገንብ

685. ሽሎተን ፔእደ አትያ ተመ አቸን ፔእደ በሽያ ተነ ሃታ ኡሽ ገውሱ

. ችሎት የዋለች እንስራ እሳት ላይ የዋለችዋን ምጣድ ውሃ አጠጪኝ ትላለች

.. የደላው ሙቅ ያኝካል

.. የበላን ያብላላዋል

.. ማኅበር የዋለች እናት ዛሬም ይርባቸዋልን ትላለች

686. ሽር ቤእን ሻቴ ሻቴከ፣ መጥ ከትንክ ሰንት ሰንተ

. አገላብጠው ቢያዩት ጣባ ጣባ ነው፤ ለቅመው ቢያዘጋጁትም ጉመን ጉመን ነው

.. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

687. ሽንቅያ ላፊ ኡረይ መተን መተን ማነ ጌስ

. ትንሽ ስንቅ የያዘ ሰው በቅርቡ እንብላ ይላል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

.. በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው

688. ሽየይ ሺምፑዋረ ዴአይስ ጋነው ጩወቴስ

. አር ነፍስ አለኝ ለማለት ይጨሳል

.. ወግ ነው ሲ.ዳሩ ማልቀስ፣

689. ሽያ ሾሮይ ዶአ ሾሩዋ በይዜስ

. የአር ጉረቤት የአውሬን ጉረቤት ያበላሻል

.. ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፊስ ትማራለች

.. ቂጢኛም ከውርዴ ጋር ይውላል

690. ሽይድ ይየ እሶይ ሽየነው ብየ ላፑና ጦኔስ

. ተፀዳድቶ የሚመጣ አንድ ሊፀዳዱ የሚሄዱትን ሰባት ያሸንፋል

.. ሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ

.. ላምሳ ጋን አንድ አለሎ

691. ሽግቼነን ሚደ ጌሌሽያ ቂፈውሱ

. ሳታሽ የበላች ዝንኸሮ ትስላለች

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም

692. ሽግቼነን ባርደ ጌሌሾይ ቁፍ ሀይቂስ

. ሳያሽ የጐረሰ ዝንዠሮ በሳል ይሞታል

.. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

693. ሼሌቂ ሼንዴረይ ቃትሽን ሜሌስ

. የቀባጭ ገንፎ እያማሰለችው ይደርቃል

.. የቀበጠ ሰው ከሞት ይደርሳል

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

694. ሼምፔነ ኩሼ ሽያ ካሼስ

. የማያርፍ እጅ አር ይዝቃል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች

695. ሼምፖይ ሻጭድ መልዱዋ ሜስ

. ነፍስ (ህይወት) ከከረመ ዘንጋዳ ይበላል

.. መኖር ደጉ ሁሉን ያሳያል

696. ሼምፖይ ሻጭድ ሼንዴራ ሜስ

. ህይወት ከርሞ ገንፎ ይበላል

.. ፈሪ ለናቱ ያገለግላል

.. የትዕግስት ፍሬ ጣፋጭ ነው

697. ሼምፖይ ዴእዮ ኡር ኡበባ ቤኤስ

. ህይወት (ነፍሱ) ያለ ሰው ሁሉን ያያል

.. እድሜ መስተዋት ነው

698. ሼምፖይ ዴኤስ ጊድ ሸየይ ጩወቴስ

. እር ነፍስ አለኝ ብሎ ይተነፍሳል

.. አልሞት ባይ ተጋዳይ

.. ሰው መሳይ በሸንጐ

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

699. ሼሸው ክዩነ ጌድያ ሶሄተደ ቀሼተውሱ

. ለሽንት ወደውጪ የማይወጣውን እግር ታሽታ ትታሰራለች

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

.. ሲሞቱ ቢያይ ያንቀላፋል

700. ሺሸው ጉፍየን በውሽን ግየው ፐርሱዋ አገነ ገውሱ

. ለሽንት በምርኩዝ የምትሄድ መሸታ ጠላ እጠምቃለሁ ትላለች

.. አቅምን አለማወቅ

.. ከአቅም በላይ መንጠራራት

701. ሼንዴረይ ኡሉወውኔ ኪሀ፣ ሀርግየውኔ ኪሀ

. ገንፎ ለሆድ ጥጋብም ለበሽታም ጥሩ (መድኃኒት) ነው

.. ገንፎ ለጉንፋን መድኃኒት ነው እግረ መንገዱን ለሆድ ይበጃል

702. ሼኔ አወ አፎራ ዩድድ በው ገጣን አቴስ

. ንዴት ባለቤቱን ገደል ሰድዶ ብቻውን ይቀራል

.. ንዴት ባለቤቱን ይጐዳል

703. ሼክ ግዮ ገድያ ባኔ ሼንዴራ ማኔ ግን ሼከ ባነ ጊድ ከእደ ሼንዴራ አግድ አግና እግያ ሄሜቴስ

. ሼካ የተባለ አገር ትሄዳለህ ወይስ ገንፎ ትበላለህ ቢለው ሼካ እሄ ዳለሁ ብሎ የበሰለ ገንፎ ሳይበላ ወጥቶ የወር መንገድ ይጓዛል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. ልፋ ያለው በህልሙ ስልቻ ይሸከማል

704. ሼኪ ሙቴ ሼንዴር ሙቴ

. (ሼኪ) ድርቅና ይቀርባል ወይስ ገንፎ ይቀርባል

.. ከእጇ በጉንጬ

705. ሾሩወው ኪህየ ጌለእያ ሶን ዬለውሱ

. ለጉረቤት የምትቸገር ልጃገረድ እቤት ትወልዳለች

.. ይሉኝታ የራስ ዓሊን ቤት የፈታ

.. አይነ አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች

706. ሾሩዋ ሞትያረ ገድያ ቄጥያረ

. ጉረቤት የምትሞግት ሜካ የምትመነጥር

.. ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጉረቤት

707. ሾሮ በለይ ጌድያ ናኣ ሜጭሲስ

. አጉል ጉረቤት እግር ሁለቴ ያሳጥባል

.. ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሁል ጊዜ ሲያለቅስ ይኖራል

708. ሾሮ ጌለእየ ሾሮ ዎደላ ጌለውሱ

. የጉረቤት ልጃገረድ የጉረቤት ጉረምሳ ታገባለች

.. ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ

.. ለይቶት አባ ንጉሷ

709. ሾሸይ ሾጭ ዬግን ጎይና ቃቴስ

. እባብ ደብድበው ሲጥሉት ጅራቱን ያነቃንቃል

.. ቂሙን አይረሳም

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

710. ሾሸይ እሱዋ ሞርን አሰይ ሄዛ ሞሬስ

. እባብ አንዴ ሲያጠፋ ሰው ሦስቴ ያጠፋል

.. ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው

711. ሾሻ ሁጳያ ጉተ ጊድ ዬድ ኤሬቴነ

. እባብ ትንሽ ነው ተብሎ ጭንቅላቱ አይረገጥም

.. ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ

.. ሙያ በልብ

712. ሾሻ ኤርድ ጌድያ ድጌስ

. እባብን አውቆ እግር ነሳው

.. እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው

713. ሾቢያ ፐርሱዋ ሾፐይ ገኔስ

. የግብገሆን ጠላ ደህና አድርጎ ይጠጣል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. የሰውን ባህያ የራስን በጉያ

714. ሾጼ ሶ ጌልድ ደዌ ግዴስ

. እንቁራሪት እቤት ገብቶ ዘንዶ ይሆናል

.. በእጅ አግብቶ ቁንጣን

.. እቤት የገባ ውሻ ባለቤቱን አትግባ ይላል

715. ሾጼ ጋሞተ ጣገነ ጊድ ጡቅ ሀይቁስ

. እንቁራሪት እንደአንበሳ አገሳለሁ ብሎ ፈንድቶ ይሞታል

. እንቁራሪት ገዞን አክል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች

.. አቅሙን አያውቅ

716. ሾጩነ አስ ግተ ምታ ቶኬስ

. የማይመታ ሰው ትልቅ እንጨት (ዱላ) ይሸከማል (ያነሳል)

.. የፈሪ ዱላ ዘጠኝ ነው

## ቀ

717. ቀመ ሼሸይ አይቅን ኩሽየውኔ ኢ.ተ፣ ስንግን ሲ.ርየውኔ ኢ.ተ

. የሌሊት ሽንተ (አር) ቢይዙት ለእጅም መጥፎ ነው፣ ቢያሸቱት ለአፍንጫም መጥፎ ነው

.. የባለጌ ምራቅ ከፍ ሲል እደረቱ ዝቅ ሲል እጉልበቱ

.. የማታ ሩጫ እንቅፋት ትርፉ

718. ቀመ ቀረይ ተ አዝና ገውሱ ከይሱዋ መችያ

. የሌሊት ጀግና ባሌ ነው ትላለች የሌባ ሚስት

.. ለራስ ሲ.ቆርሱ አያሳንሱ

.. የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ

719. ቀመ ቤተነ ኦሰንችያ ገለስ የሼስ ገውሱ

. ሌሊት የምትጠፋ አሽከር ቀን ፈራሁ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

.. ዶሮዋን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት

720. ቀመ ቤትያ ባናረ ገለስ ፐራ ቤአደ ተነ ማነ ገውሱ

. በጨለማ ጠፍታ የምትሄድ ቀን ፈረስ አይታ ይኸ ይበላኛል ትላለች

.. ሞኝ አይታወቅብኝም ባይ

721. ቀመ ከይሶተናረ ገለስ የሼስ ገውሱ

. ማታ የምትሰርቅ ቀን እፈራለሁ ትላለች

.. ሞኝ አያውቅብኝ ባይ

722. ቀመ ውቅያረ ገለስ ተነ የሼስ ገውሱ

. ማታ የምትሰርቅ ቀን እፈራለሁ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

.. አስመሳይ፣ ሰው መሳይ በሸንኮ